# የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት

# ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ

**319/2013**

የካቲት 2005
አዲስ አበባ

# የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ

## መግቢያ

አገራችን ላለፉት ዘጠኝ ተከታታይ አመታት በማስመዝገብ ላይ ያለችውን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት ለማረጋገጥ መንግስት ካስቀመጣቸው ግቦች መካከል የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ገቢ ማሳደግ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ለዚሁም ግብ ስኬት ወሳኝ ሚና የሚኖረውን የወጪ ንግድን ማሳደግ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልከው በአብዛኛው የግብርና ምርቶች ሲሆኑ መጠናቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ የኤክስፖርት ንግዳችን ከዚህም ሰፋ ብሎ የማኑፋክቸሪንግ ምርቶችን ጨምሮ እያደገ እንደሚሄድ የሚጠበቅ ሲሆን ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ቀጣይነት ለማስጠበቅ እና ዘርፉን ለማሳደግ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አሠራራቸውን አቀናጅተው የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ዘላቂ የክትትልና የድጋፍ ማዕቀፍ ቀርጸው መንቀሳቀስ የሚኖርባቸው ሲሆን ሌሎች ባለድርሻ አካላትም በአሠራር ላይ የሚታዩ ችግሮችን በወቅቱ ለመፍታት የየበኩላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

በመሆኑም የአገራችንን የውጭ ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ አንዱ የትራንዚት ወጪና ጊዜን ለመቀነስ የሚያስችል የትራንዚት ሥርዓት መመሪያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የአገሪቱ የወጪ ንግድ በተፈላጊ ደረጃ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱ የተረጋገጠ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ የወደብና የትራንዚት አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል የአሠራር መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ መስኩ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነቱ እንዲረጋገጥ የሚመለከታቸው አካላት የተቀናጀ እና የተሳለጠ የአሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ገብተው እንዲሠሩ ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

በዚህ ሂደት ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች መካከል በወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን በመፍታት በዘላቂነት ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚመራበትን ሥርዓት የመዘርጋት አስፈላጊነት ታምኖበታል፡፡ የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓቱ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ወሣኝ የሆኑና በትራንዚት ትራንስፖርት ሂደቱ እያጋጠሙ ያሉትን በቀጣይም ሊከሰቱ የሚችሉ ተግዳሮቶችን ግምት ውስጥ ያስገባ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስያዝ የግድ ይላል፡፡

በዚህ መሠረት የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት ሥርዓት የሚመራበትን አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው አካላት እስካሁን ተግባራዊ እያደረጉ የቆዩት ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የወጪ ንግድ ልማት መስኩ የታለመለትን ዓላማ ያሳካ ዘንድ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነቶችና ግዴታዎች ለመወሰን በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) ለሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

2.1 **ወጪ ደረቅ ዕቃ** ማለት በኮንቴይነርና በብትን ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች የሚላኩ ቡና፣ ጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች ፤ ልዩ ልዩ የኢንዱስትሪ ምርቶች እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤

2.2. **የባንክ ፈቃድ** ማለት ማንኛውም ላኪ ዕቃዎችን ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ ሀገራት ለመላክ ከባንኮች የውጭ ምንዛሬ ፈቃድ እና ሌሎችንም ድጋፍ የሚያገኝበት ስርዓት ነው፡፡

2.3. **የዕቃ አስተላላፊነት ውክልና** ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይን ወይም ዕቃ ላኪን በመወከል የጉምሩክ፤ የወደብ እና ሌሎች ተያያዥ ሥነ-ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጪ ዕቃዎች በወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ ማድረግ ሲሆን ዕቃን የማጓጓዝንና የማስረከብን ሥራ ይጨምራል፤

2.4. **ዕቃ አስተላላፊ** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 መሠረት የዕቃ አስተላላፊነት ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.5. **የመርከብ ውክልና** ማለት የመርከብ ባለንብረትን፤ ተከራይን፤ ወይም አከናዋኝ በመወከል፤ መርከቡ የሚያጓጉዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ ማግኘትንና መመዝገብን፤ በባህር ወደብ ላይ እና በአገር ውስጥ ለመርከቦች አገልግሎት መስጠትን፤እንዲሁም መሰል ተግባራት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

2.6. **የመርከብ ወኪል** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 መሠረት የመርከብ ውክልና ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.7. **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት** ማለት በደንብ ቁ. 37/1990 በተወሰነው እና የትራንስፖርት ሚኒስቴሩ ወደፊት በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሰረት በዕቃ አስተላላፊነት ፣ በመርከብ ውክልና ፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ የተመለከቱ የንግድ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የሚያበቃ የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች እና የቢሮ አደረጃጀት መሟላቱን በማረጋገጥ በባለስልጣኑ የሚሰጥ ማስረጃ ነው፤

2.8. **የኮንቴይነር ጭነት ማስተናገጃ ጣቢያ ወይም** /container freight station/ (CFS) ማለት ዕቃ በኮንቴይነር የማሸግ (stuffing) ወይም ከኮንቴይነር የማስወጣት (un-stuffing) እና ሌሎች መሰል ተያያዥ አገልግሎቶች የሚሰጡበት ቦታ ነው፤

2.9. **ድርጅት** ማለት የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 የተቋቋመው የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

2.10. **አዋጅ** ማለት የማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 ነው፤

2.11. **ሚኒስቴር** ወይም **ሚኒስትር** ማለት እንደቅደምተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2.12. **ባለሥልጣን** ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤

2.13. **ታሪፍ** ማለት የዕቃ አስተላላፊ ወይም የመርከብ ወኪል ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት በወጪ ደረቅ ጭነት ትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪነት የተሰማሩ አከናዋኞች ከዕቃ ላኪ ጋር ውል በገባበት ጊዜ የሚጠቀምበት የውል ሁኔታ ሆኖ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠይቀውን የአገልግሎት ክፍያ የሚጨምር ነው፤

2.14. **ሰው** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ ቀጥሎ የተመለከቱት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

3.1 የሀገሪቱን የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜና ወጪ ለመቀነስ፣

3.2. የሚመለከታቸውን አካላት ኃላፊነት ለመወሰንና አሰራራቸውን ለማቀናጀት ፤

3.3. የአገልግሎት ሰጪ አከናዋኞችን አገልግሎት አሰጣጥ እና አሠራር ለመቆጣጠር፣

3.4. ለወጪ ዕቃዎች በባህር ወደብ ላይ የሚከፈለውን አላስፈላጊ የሆነ የውጭ ምንዛሬ ለማዳን፣

3.5. የሀገሪቱ የወጪ ዕቃዎች በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጎ ለመላክ የሚያስችል አሠራር ለመተግበር፣

3.6. የመንገድ ላይ የዕቃዎች ጉዳት ለመቀነስና የዕቃዎችን ደህንነት ለማስጠበቅ

3.7. በባህር ወደብ የወጪ ዕቃ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ቆይታ ጊዜ ለመቀነስ የሚያስችል ሥርዓት ለመተግበር ነው፡፡

## 4. አስፈጻሚ አካል

በአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 8፣ 19 ሥር በተደነገገው መሠረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓትን ለመወሰን የወጣውን ይህንን መመሪያ የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከኢትዮጵያ ተንጉዘው በባህር ወደብ በኩል ወደ ውጭ ሀገራት በሚላኩ የወጪ ደረቅ እቃዎች ላይ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## መመሪያው የሚመለከታቸው አካላት ሃላፊነትና ተግባር

### 6. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ተግባርና ሃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

6.1. የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ስታንዳርዱን ያሻሽላል፡፡

6.2. የወጪ ደረቅ ዕቃዎች የትራንዚት አገልግሎት ስርዓት በሚመለከት፤ የትራንዚት ትራንስፖርት ወጪ /Transit Transport Cost/ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

6.3. በሀገር ውስጥ በዕቃ አስተላላፊነት ውክልና፣ በመርከብ ውክልና የአገልግሎት መስክ የተሰማሩትን እና ወደፊት ወደ መስኩ ለመግባት ማመልከቻ የሚያቀርቡትን በመገምገም፣ ብቁ የሆኑትን በመለየት የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የተሰጣቸውን አከናዋኞች የተመለከተ ወቅታዊ መረጃ እያደራጀ ለላኪዎች፣ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ለንግድ ሚኒስቴር፣ ለወደብ ባለስልጣናት እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ይሰጣል፡፡

6.4. ለአገልግሎት ብቁ መሆናቸው የተረጋገጡ የዕቃ አስተላላፊ ኩባንያዎች ከእነርሱ ጋር በየባህር ወደቦች ተቀናጅተው የሚሰሩትን የውጭ ሀገር የእቃ አስተላላፊ ኩባንያዎች ስምና ውል እንዲያስመዘግቡ ያደርጋል በውሉ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ይከታተላል፤ ከውሉ ጋር የተያያዘ ችግር ሲያጋጥም ከሀገራቱ ጋር በሚኖር የሁለትዮሽ ስምምነት መሰረት ችግሮችን ይፈታል፡፡ መረጃውንም በየጊዜው ወቅታዊ ያደርጋል፡፡

6.5. የእቃ አስተላላፊዎች፣ የመርከብ ወኪሎችና ሌሎችንም የብቃት ማረጋገጫ ማደስና ብቁ ያልሆኑትን የመሰረዝ ተግባር ያከናውናል ለዚህም የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

6.6. ባለስልጣኑ በሚያወጣው የቁጥጥር እና ክትትል መርኃ-ግብር መሠረት በሚደረግ ግምገማ የመመሪያውን ዓላማ በማሳካት ረገድ የላቀ አፈጻጸም ያስመዘገቡ አገልግሎት ሰጪዎች ተገቢውን ማበረታቻ እና ዕውቅና ይሰጣል፡፡

6.7. የብቃት ማረጋገጫቸው የታገደባቸውን /የተሰረዘባቸውን/ የዕቃ አስተላላፊዎች፣ የመርከብ ወኪሎችና ሌሎችንም አገልግሎት ሰጪዎች ዝርዝር ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች እና ተጠቃሚዎች በየወቅቱ ያሳውቃል፡፡

6.8. የወጪ ደረቅ ዕቃዎችን በተመለከተ በባህር ወደብ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን መለየት፣ እንዲሁም የወደብና የትራንዚት አገልግሎት በሚሻሻልበት ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ድርድር እና ምክክር በማድረግ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል፡፡

6.9. ስልታዊ የሆነ ሀገራዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋትና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመደገፍ በየዕለቱ ከዕቃ አስተላላፊዎች እና ከመርከብ ድርጅት ወኪሎች የወጪ ደረቅ ጭነት መጠን በዕቃ ዓይነት በመለየት እንዲሁም በኦፐሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ዕለታዊ መረጃ ይሰበስባል ያጠናቅራል፡፡

6.10. ተቆጣጣሪ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን እንዲሁም በሂደቱ ውስጥ ወሣኝ ሚና ያላቸው አካላት በተበታተነ ቦታ የሚሰጡትን አገልግሎት በኮንቴይነር ማስተናገጃ ቦታ /በCFS/ ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግና ወደ አንድ መስኮት አገልግት "one window shop" አሠራር በመለወጥ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

6.11. የኮንቴይነር አቅርቦት መረጃ ማዕከል እንዲደራጅና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

6.12. በደረቅ ወደቦችና በሌሎች የኮንቴይነር ማስተናገጃ /CFS/ ውስጥ የመርከብ ወኪሎችና የዕቃ አስተላላፊ ኩባንያዎችን የሥራ ድርሻና አጠቃላይ የወጪ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ አሽጎ በመላክ ሂደት የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

6.13. በሎጅስቲክስ ዘርፍ የተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች በወጪ ንግድ ላይ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

6.14. ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እየተከታተለ ለሚኒስቴሩና ለሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ይልካል፡፡

## 7. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተግባርና ሃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

7.1. የወጪ ንግድን በተመለከተ ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ከሚላክለት የዕቃ አስተላላፊዎች ዝርዝር ውጪ ሌሎች በዚህ አገልግሎት እንዳይሰማሩ ይቆጣጠራል፡፡
7.2. የወጪ ዕቃ መረጃ በወቅቱ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይሰጣል፡፡
7.3. የባዶ ኮንቴይነር ነፃ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚያስችል አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
7.4. የወጪ ደረቅ ዕቃ ትራንዚትን በተመለከተ ከጉምሩክ አሰርር ጋር የተያያዙ ማነቆዎችን ይፈታል፡፡

## 8. የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ተግባርና ሃላፊነት

ድርጅቱ በዕቃ አስተላላፊነትና በመርከብ ውክልና አገልግሎት ሰጪነቱ የሚጠበቅበት ግዴታና ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

8.1. በሀገር ውስጥ ለወጭ ንግድ አገልግሎት የሚውል የባዶ ኮንቴይነር አቅርቦት እንዲኖር ያመቻቻል፡፡
8.2. በሀገር ውስጥ በሚገኙ ተርሚናሎች ወጪ ንግድን ለመደገፍ እንዲቻል ለባዶ ኮንቴይነር ከመጋዘን ኪራይ ለበቂ ጊዜ (Reasonable time) ነፃ የሆነ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
8.3. በሀገር ውስጥ ወደ ተመረጡ የኮንቴይነር ጭነት ማስተናገጃ ጣቢያዎች /CFS/ ያለምንም ክፍያ ባዶ ኮንቴይነር አጓጉዞ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
8.4. በመንግስት በሚሰየሙ የኮንቴይነር ጭነት ማስተናገጃ ጣቢያዎች /CFS/ ወጪ ዕቃዎች በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጎ ለመላክ የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎች እንዲሁም የአሠራር ሥርዓቶችን የማሟላል፡፡

## 9. <u>የዕቃ አስተላላፊዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ. 37/1990 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ማናቸውም የዕቃ አስተላላፊ የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

9.1. አግባብ ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና በዚህ የወጪ እቃዎች የትራንዚት ሥርዓት መመሪያና ባለስልጣኑ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሠረት የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

9.2. ባዶ ኮንቴይነር የሚቀርብበትን ሁኔታ የማመቻቸት፤ ላኪው የተሻለ አማራጭ እንዲጠቀም የማማከር ሙያዊ ግዴታ አለበት፡፡

9.3. ላኪውን በመወከል የወደብ ታሪፍና በትራንዚት ሂደቱ ውስጥ የሚኖሩ የሶስተኛ ወገን ታሪፎችን የመቆጣጠርና ተገቢነት የሌለው ወጪ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡

9.4. በባለስልጣኑ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት መደበኛ ሪፖርት እና ትክክለኛ መረጃ የማቅረብ እንዲሁም የመረጃ ለውጡን ወቅታዊ የማድረግ እና ኦፕሬሽን ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለማሪታይም ጉዳይ ባስልጣን በወቅቱ ያሳውቃል፡፡

9.5. ለላኪው የተሟላ መረጃ የመስጠት ፣በወቅቱ አስፈላጊ ሰነዶችን (Bill of Loading) የማቅረብ (የማስረከብ) እና ላኪው በተሟላ መረጃ ላይ ተመስርቶ የላኪነት ሥራውን እንዲሰራ ይደግፋል፡፡

9.6. አስመጪዎችን በመወከል ገቢ ዕቃዎችን የያዘ እና ከወደብ የመጣውን ኮንቴይነር የመርከብ ድርጅቱ ወኪል ኮንቴይነሩን ለወጪ ንግድ የሚፈልገው መሆኑን በፁሁፍ ከገለጸለት ባዶ ኮንቴይነር ወደ ወደብ እንዳይመለስ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## 10. የመርከብ ወኪል ተግባርና ሃላፊነት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ በተመለከተ ማንኛውም የመርከብ ወኪል የሚከተለው ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

10.1. አግባብ ባላቸው ሕጎች፣ ደንቦችና በዚህ የወጪ ደረቅ ዕቃ የትራንዚት ሥርዓት መመሪያና ባለስልጣኑ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሠረት ይሰራል፡፡

10.2. ወኪል የሆነበትን የመርከብ ኩባንያ የወደብ ፕሮግራም የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ ለውጦች ለባለስልጣን መ/ቤቱ ይሰጣል፡፡

10.3. በሚወክለው የመርከብ ኩባንያ የተጓጓዘ የኢትዮጵያ ጭነት መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለሰልጣን እና ለደንበኞች የመስጠትና የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

10.4. ወደ ሀገር ውስጥ የተጓጓዙ ኮንቴይነሮችን ለወጪ ደረቅ ዕቃዎች አገልግሎት ያቀርባል ፤ያመቻቻል፡፡

## 11. ንግድ ሚኒስቴር ተግባርና ሃላፊነት

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴር የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

11.1. የወጪ ዕቃዎች ዝርዝር ዓመታዊ እቅድ ከዝርዝር የሎጅስቲክስ አቅርቦት ፍላጎት ጋር የበጀት ዓመቱ በገባ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይልካል፡፡

11.2. ከባለስልጣኑ ወይም ከሚኒስቴሩ ብቁ የዕቃ አስተላላፊና የመርከብ ወኪል ኩባንያዎች ዝርዝር ሲደርሰው ለላኪዎች ያሳውቃል፡፡

11.3. የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓትን በተመለከተ የሚወጡ መመሪያዎች፣ ውሣኔዎችና መሠል መረጃዎችን ለላኪዎች ያሳውቃል፡፡

11.4. ከባለስልጣኑ በሚደርሰው መረጃ መሠረት የአፈፃፀም ብቃታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነሱ ምክንያት ሥራቸውን በአግባቡ የማይወጡ ዕቃ አስተላላፊዎች እና የመርከብ ወኪሎች የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሠርዛል ፣ለባለሰልጣኑ እና ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ያሳውቃል፡፡

11.5. ከወጪ ደረቅ ዕቃዎች ትራንዚት ሂደት ጋር የተያያዙ የንግድ ሥርዓት ማነቆዎችን ተከታትሎ ይፈታል፡፡

## 12. የማስፈጸሚያ ስልቶች

ከዚህ መመሪያ ጋር በክፍል ሶስት አባሪ ሆነው የተያያዙት የወጪ ደረቅ እቃዎች ትራንዚት አገልግሎት ሥርዓት አፈጻጸም ስታንዳርዶች ማለትም ፡-

12.1. በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጎ የሚላክ ደረቅ ጭነት ኦፕሬሽንን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን፤

12.2. በባሕር ወደብ በኮንቴይነር ታሽጎ የሚላክ ወጪ ዕቃን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን ስታንዳርድ የመመሪያው አካል ሆነው ይፈጸማሉ።

## 13. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

**ይህ መመሪያ ከዛሬ ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።**

**አዲስ አበባ--------ቀን 2005 ዓ.ም**

*ድሪባ ኩማ*

*የትራንስፖርት ሚኒስትር*

# ክፍል ሶስት

## የወጪ ደረቅ ጭነት  ትራንዚት አገልግሎት ሥርዓት አፈጻጸም ስታንዳርድ

### መግለጫ

የወጪ ደረቅ ዕቃዎችን  ትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያን ለማስፈጸም እና በመመሪያው ውስጥ ሃላፊነትና ተግባር የተሰጣቸው አካላት  ኃላፊነቶቻቸውን  በአግባቡ ማከናወናቸዉን  ለመከታተልና አፈጻጸማቸውን ለመለካት እንዲያስችል ይህ ወጥ  የሆነ የወጪ ደረቅ ዕቃዎች  ትራንዚት ትራንስፖርት ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡

ስታንዳርዱ ሲዘጋጅ በዋናነት መሰረት ያደረገዉ በወጪ የደረቅ ጭነት ዕቃዎች ትራንዚት ትራንስፖርት  ጊዜ እና ወጪን ከመቀነስ አንጻር  የተደረገ ጥናትን፣ በዚህ ደረጃ በጥናት የተገኘውን አማካይ ውጤት መሰረት በማድረግ ፤ በስታንዳርዱ ላይ የዘርፉ ተዋናይ አካላትን አስተያት በማካተት እና የፈጻሚ አካላትን ስምምነት  በመዉሰድ ነዉ፡፡

በመሆኑም ስታንዳርዱ የስራው ሂደት የሚወስደውን ጊዜ እንዲሁም የተግባሩን ፈጻሚ አካል በግልጽ በማስቀመጥ እና ዕቃዎች በኮንቴይነር ታሽገው የሚነሱበትን ቦታ መሰረት በማድረግ በሁለት ደረጃ በመለየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 12.1. በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር ታሽጎ ለሚላክ ወጪ ደረቅ ዕቃዎች ኦፐሬሽን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

| ተ/ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 1 | በባንክ የሽያጭ ውል በማስመዝገብ እስከ ባንክ ፈቃድ ማግኘት እና የወጪ ዕቃ ዝርዝር ዕቅድ የጭነት ትዕዛዝ (shipping Instruction) ከመሰጠቱ አንድ ወር /30 ቀናት/ አስቀድሞ ለዕቃ አስተላላፊዎች ያሳውቃል፣ | የጭነት ትዕዛዝ ከመስጠት 30 ቀናት አስቀድሞ፣ | ላኪ |
| 2 | በአንድ ሣምንት ውስጥ የሚፈለገው የኮንቴነር ዓይነትና መጠን፣<br>• በሀገር ውስጥ መኖሩን<br>• በሀገር ውስጥ ከሌለ በባህር ወደብ መኖሩን፣<br>• በባህር ወደብ ከሌለና በታቀደው ጊዜ ሊኖር የማይችል መሆኑን አረጋግጦ አማራጭ የውሳኔ ሃሳብ ለላኪው ያቀርባል። | ከላኪ የጭነት ዕቅድ መረጃ በደረሰው በአንድ ሣምንት ውስጥ፣ | የእቃ አስታላላፊው |
| 3 | ከዕቃ አስተላላፊው የተገኘን መረጃና ሙያዊ አስተያየትን መሠረት በማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዕቃው ተቀባይ /ገዥ/ ጋር በመነጋገር አመቺ የሆነ የጭነት ትዕዛዝ ከተሟላ መረጃ ጋር ይሰጣል፣ | ከዕቃ አስተላላፊ የተላከ የኮንቴይነር አቅርቦት መረጃ በተላከ በሶስት ሣምንት፣ | ላኪ |
| 4 | ከተሟላ ሰነድ ጋር የጭነት ትዕዛዝ (shipping Instruction) ይሰጣል፣ | 1 ሰዓት | ላኪ |
| 5 | ባዶ ኮንቴይነር እንዲቀርብ የመርከብ ወኪልን ይጠይቃል | 1 ሰዓት | ዕቃ አስተላላፊ |
| 6 | ባዶ ኮንቴይነር ለጠያቂ ዕቃ አስተላላፊ በተጠየቀው የባዶ ኮንቴይነር ማስተናገጃ ጣቢያ (CFS) እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ያስተላልፋል፣ | 1 ሰዓት | የመርከብ ወኪል |

| ተራ ቁጥር | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 7 | ባዶ ኮንቴይነር ያቀርባል፣ | ከ½ - 1ቀን | ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ |
| 8 | የጉምሩክ ዲክለራሲዮን ማዘጋጀት፣ የወደብ ትመና ማዘጋጀትና ሰነድ ለጉምሩክና በወደብ ለሚገኝ ዕቃ አስተላላፊ መላክ | ½ ቀን | ዕቃ አስተላላፊ |
| 9 | ዲክለራሲዮን መቀበልና የፍተሻ ፈቃድ መስጠት | 1 ሰዓት | ኢ.ገ.ጉ.ባ |
| 10 | የዕቃ ደረጃና ጥራት ሰርተፊኬት መስጠት | ግማሽ ቀን | ንግድ ሚ/ር |
| 11 | ዕቃን በኮንቴይነር የማሸግ (Stuffing) ስራ ያከናውናል | 3 ሰዓት(ለ1 ኮንቴይነር) | ዕቃ አስተላላፊ |
| 12 | የመንገድ ወረቀት ይሰጣል | 1/2 ሰዓት | ኢ.ገ.ጉ.ባ |
| 13 | ጭነቱን ተረክቦ ያጓጉዛል | 2 ½ ቀን | ዕቃ አስተላላፊ /ትራንስፖርተር |
| 14 | ጭነት መድረሱን ተከታትሎ የወደብ ፎርማሊቲ በማጠናቀቅ ለመርከብ ወኪል ማስረከብ እና የጭነት ዝርዝር ለወደብ መስጠት | 1 - 2 ቀን | የሀገር ውስጥ ዕቃ አስተላላፊ /የባለ ባህር ወደብ ዕቃ አስላላፊ |
| 15 | ዕቃው በመርከብ ላይ እንዲጫን ተከታትሎ ማስፈጸም | 1-7 ቀን | የሀገር ውስጥ ዕቃ አስተላላፊ |
| 16 | የጭነት ሰነድ(Bill of Loading) አዘጋጅቶ መላክ | 1-2 ቀን | የሀገር ውስጥ ዕቃ አስተላላፊ |
| 17 | ጭነቱ ወደ መድረሻ ወደብ ማጓጓዝ | የተለያየ | የመርከብ ኩባንያ |

## 12.2. በባህር ወደብ በኮንቴይነር ታሽጎ ለሚላክ የወጪ ደረቅ ዕቃዎች ኦፐሬሽን በተመለከተ ተፈጻሚ የሚሆን

| ተ/ቁ | የትራንዚት ፕሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 1 | በባንክ የሽያጭ ውል በማስመዝገብ እስከ ባንክ ፈቃድ ማግኘት እና የወጪ ዕቃ ዝርዝር ዕቅድ የጭነት ትዕዛዝ (shipping Instruction) ከመሰጠቱ አንድ ወር /30 ቀናት/ አስቀድሞ ዕቃ አስተላላፊ ያሳውቃል፣ | የጭነት ትዕዛዝ ከመስ ጠት 30 ቀናት አስቀ ድሞ፣ | ላኪ |
| 2 | በአንድ ሣምንት ውስጥ የሚፈለገው የኮንቴነር ዓይነትና መጠን፣<br>• በሀገር ውስጥ መኖሩን<br>• በሀገር ውስጥ ከሌለ በጅቡቲ ወደብ መኖሩን፣<br>• በባህር ወደብ ከሌለና በታቀደው ጊዜ ሊኖር የማይችል መሆኑን አረጋግጦ አማራጭ የውሳኔ ሃሳብ ለላኪው ያቀርባል፡፡ | ከላኪ የጭነት ዕቅድ መረጃ በደረሰ በአንድ ሣምንት ውስጥ፣ | ዕቃ አስተላላፊ |
| 3 | ከዕቃ አስተላላፊ የተገኘን መረጃና ሙያዊ አስተያየትን መሠረት በማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዕቃው ተቀባይ /ገዥ/ ጋር በመነጋገር አመቺ የሆነ የጭነት ትዕዛዝ ከተሟላ መረጃ ጋር ይሰጣል፣ | ከዕቃ አስተላላፊ የተላከ የኮንቴይነር አቅርቦት መረጃ በተላከ በሶስት ሣምንት፣ | ላኪ |
| 4 | ከተሟላ ሰነድ ጋር የጭነት ትዕዛዝ (shipping Instruction) ይሰጣል፣ | 1 ሰዓት | ላኪ |
| 5 | የጉምሩክ ዲክለራሲዮን ማዘጋጀት፣ የወደብ ትመና ማዘጋጀትና ሰነድ ለጉምሩክና በወደብ ለሚገኝ ዕቃ አስተላላፊ መላክ | 1 ሰዓት | ዕቃ አስተላላፊ |
| 6 | ዲክላራሲዮን መቀበልና የፍተሻ ፈቃድ መስጠት | 1 ሰዓት | ኢ.ገ.ጉ.ባ |

| ተራ ቁጥር | የትራንዚት ኘሮሲጀር | የጊዜ ስታንዳርድ | የሥራው ባለቤት |
|---|---|---|---|
| 7 | የዕቃ ደረጃና ጥራት ሰርተፊኬት መስጠት | ግማሽ ቀን | ንግድ ሚ/ር |
| 8 | የመንገድ ወረቀት መስጠት | 1/2 ሰዓት | ኢ.ገ.ጉ.ባ |
| 9 | ጭነቱን ተረክቦ ያጓጉዛል | 2 ½ ቀን | ዕቃ አስተላላፊ /ትራንስፖርተር |
| 10 | የወደብ  ፎርማሊቲ ማጠናቀቅ | 2 ሰዓት | የመርከብ ወኪል/ዕቃ አስተላላፊ |
| 11 | ባዶ ኮንቴይነር እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠትና የጭነት ትዕዛዝ ለወደብ ማስተላለፍ | 1 ሰዓት | የመርከብ ወኪል /ዕቃ አስተላላፊ |
| 12 | ባዶ ኮንቴይነር ማሸግ (Stuffing) | 3 ሰዓት | ዕቃ አስተላላፊ |
| 13 | ከስታፊንግ ቦታ ወደ ተርሚናል ማጓጓዝ | 2 ሰዓት | የወደብ ባለስልጣን/ የመርከብ ወኪል/ ዕቃ አስተላላፊ |
| 14 | የጭነት ዝርዝር ለወደብ መስጠት | 1 ሰዓት | የመርከብ ወኪል/ ዕቃ አስተላላፊ |
| 15 | ዕቃው በመርከብ ላይ እንዲጫን ተከታትሎ ማስፈጸም | 1-7 ቀን | የሀገር ውስጥ ዕቃ አስተላላፊ |
| 16 | የጭነት ሰነድ(Bill of Loading) አዘጋጅቶ መላክ | 1-2 ቀን | የሀገር ውስጥ ዕቃ አስተላላፊ |
| 17 | ጭነቱ ወደ መድረሻ ወደብ ማጓጓዝ | የተለያየ | የመርከብ ኩባንያ |